

# የረጅም ሕንፃ አፓርትመንት እና የጋራ መኖሪያ(ኮንዶሚኒየም) ቤት ደህንነት

**የረጅም ሕንፃ አፓርትመንት ወይም የጋራ መኖሪያ ቤት ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች አስቀድመው ማሰብ እና ለእሳት አደጋ ጊዜ ዝግጅት ማድረግ አለባቸው። በመኖሪያ ሕንፃዎ ውስጥ ያሉትን የእሳት አደጋ የደህንነት መመሪያዎችን በማወቅ እና ከጎረቤቶችዎ ጋር በጋራ በመስራት የመኖሪያ ሕንፃውን በተቻለ መጠን ከእሳት አደጋ የተጠበቀ ያድርጉ።**

- የጢስ እና የካርቦን ሞኖክሳይድ (carbon monoxide) መቆጣጠሪያዎችን በዓመት ሁለት ጊዜ ይፈትሹ።
- የእሳት አደጋ ማምለጫ እቅድ በማውጣት ልምምድ ያድርጉ።
- የተለኮሰ ሻማን ፣ በመብሰል ላይ ያለ ምግብን ወይም ተንቀሳቃሽ ማሞቂያዎችን (heaters ) በፍጹም ያለ ክትትል እንዳይተው።
- ከመተኛትዎ በፊት ሁል ጊዜ የመኝታ ክፍል በር ይዝጉ።የተዘጋ በር የካርቦን ሞኖክሳይድ (carbon monoxide) ፣ የጢስ እና የእሳት ነበልባል የጉዳይነት መጠናቸውን ለመቀነስ ይረዳል፣ በተጨማሪም ለአደጋ ጊዜ ደውል (alarm) ምላሽ ለመስጠት ተጨማሪ ጊዜ ሊሰጥዎት ይችላል።
- በአፓርታማዎ ውስጥ እሳት ከተነሳ ወዲያውኑ ወደ 911 ይደውሉ እና አፓርታማዎን ለቀው ይውጡ።ሲወጡም ያለውን በር/መስኮት ከኋላዎ ይዝጉ። ለጎረቤቶችዎ ለማሳወቅ እንዲረዳ በመውጣት ላይ እያሉ የእሳት አደጋ ደውሉን (fire alarm) በመሳብ ይደውሉ።
- መውጣት ካልቻሉ፣ ከተዘጋ በር ጀርባ ይሁኑ እና ወደ 911 ይደውሉ፣ በስልክ ለሚያናግሩት ግለሰብ (dispatcher) በቤት ውስጥ ያሉበትን ቦታ ይንገሩት።
- በአቅራቢያዎ ያለው የመውጫ ደረጃ በእሳት ወይም በጢስ ሊዘጋ ስለሚችል ሁሉንም የመውጫ ደረጃዎች ለይተው ይወቁ። የእሳት አደጋ መከላከያ ዲፓርትመንት እስካላሳወቅዎት ድረስ ከሕንፃው ለመውጣት ሊፍት (elevator) በጭራሽ አይጠቀሙ።

## ከእሳት አደጋ ለማምለጥ መሰረታዊ ነጥቦች

ውጪ ወደሚገኝ የመሰብሰቢያ ቦታ ይሂዱ እና እዚያ ይቆዩ። ወደ የእሳት አደጋ መከላከያ ይደውሉ። ከሕንፃው ውስጥ መውጣት ያልቻለ ግለሰብ ካለ ፣ ለእሳት አደጋ መከላከያ ያሳውቁ።

በእሳት በጢስ ወይም በአካል ጉዳት ምክንያት ከአፓርታማዎ መውጣት ካልቻሉ፣ ጢስ እንዳይገባ እርጥብ ፎጣዎችን ወይም አንሶላዎችን በመጠቀም የበር ዙሪያ እና የአየር ማስገቢያ ቀዳዳዎችን በመሸፈን/በመጠቅጠቅ ይከላከሉ።

ወደ የእሳት አደጋ መከላከያ ይደውሉ እና ያሉበትን ቦታ ይንገሯቸው። ያሉበትን ቦታ ለመጠቆም መስኮት በትንሹ ከፍተው ደማቅ ቀለም ያለውን ጨርቅ ያውለብልቡ። የጢሱን ሁኔታ የሚያባብስ ከሆነ መስኮቱን ለመዝጋት ይዘጋጁ። የእሳት አደጋ መከላከያ ዲፓርትመንት ረጅም ሕንፃ ወስጥ የሚኖሩ ነዋሪዎችን ከሕንፃው ለማውጣት ጊዜ ሊወስድበት ይችላል። ከሕንፃው እየለቀቁ ያሉበትን ሁኔታ ለመከታተል እንዲረዳ ከእሳት አደጋ ዲፓርትመንት ጋር ይነጋገሩ።

**ለነጻ የቤት ደህንነት ፍተሻ 311 ይደውሉ።**

www.mcsafe.com